# ምድብ ሁለት (ከ1ኛ — 3ኛ) ክፍል

## 38 ኛ ሳምንት

## ጸሎት

### ዓላማ

- ማመስገንን መማር።

### ምንባባት

-

### መግቢያ

- ከዚህ በፊት *"አባታችን ሆይ"* የሚለውን ጸሎት ተምራችኋል።
- ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር የምንገናኝበት መንገድ ነው።
- በዚህ ትምህርታችንም ስለተለያዩ የጸሎት ዓይነቶች እንማራለን።

### የክለሳ ጥያቄዎች

1.ጌታችን ለሐዋርያት ያስተማረው ጸሎት ምንድነው?

2.ጸሎቱን በግዕዝና አማርኛ ታውቃላችሁ?

3.ይሄንን ጸሎት በቀን ስንት ጊዜ ትጸልያላችሁ? የጸሎት ፕሮግራማችሁ በቀን ስንቴ ነው?

### ትምህርቱ

- እግዚአብሔርን ስለጌትነቱ እናከብረዋለን፣ እናመልከዋለን ስለስጦታዎቹም እናመሰግነዋለን።የሚስፈልገንን እንዲሰጠን የተለያዩ ነገሮችን እንዲያደርግልንም እንጸልያለን።ስንጸልይም ስላደረገልን ሁሉ እግዚአብሔርን ማመስገንን ማስታወስ አለብን።
- በጠዋት ስትነሡ በሰላም ስላሣደራችሁ አመስግኑት ማታም ስለረዳችሁና፣የተባረከ ቀን ስለሠጣችሁ እና እንድትጠቀሙ በት ስለረዳችሁ ማመስገንን አትርሱ።
- ከመ መ ገባችሁ በፊትና ተመግባችሁ ስትጨርሱም ምግብ ስለሰጣችት አመስግኑ።የአመስጋኙን ለምጻም ታሪክ ታስታውሳላችሁ? ጌታ አሥር ለምጻሞች እንዲያድኑት ለምነው አዳናቸው።ነገር ግን ከእነርሱ አንዱ ብቻ እያመሰገነ ተመለሰ።አመስጋኙ ሲመለስም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ አለ _***"የዳኑት አሥሩ አልነበሩምን? አንዱ ብቻ እግዚአብሔርን ለማክበር መጥቶልና"***
- ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር የምንነጋገርበት መንገድ ከሆነ ሁሌም ልናመሰግነውና የምንፈልገውን ልንጠይቀው ይገባል። ሁሌም ስላደረገልን ነገር ልናመስግነውም ይገባል።
- የሚመግቡን፣የሚያሳድጉንና የሚያስተምሩን ቤተሰቦቻችንንም ማመስገን አለብን። የሚያስተምሩንን መምህራንና መልካም ስብዕና እንዲኖረን የምታስተምረንንም ቤተክርስቲያን ልናመሰግን ይገባል።

### መዝሙ ር

አማን በአማን (4)

መ ንግሥ ተ ሥ ላሴ ዘለዓለም ።

**ይቆየን።**